By: Cosmos-2000
Stockton, June, 2009

## ፅንስ

የርሱ መርህ የዚያ መርህ
መርህ ብቻውን ኖሮ አያውቅም
ያጨራርሳል ያስማማልም
ለግል ዝና ላገር ጥቅም ወይም
አመለካከቱ ሳይጠረብ
ሕዝባዊ ስርዬት ቢኖር

ብናየውም ተነጣጥሎ ተኮልኩሎ
በአየር ላይ ተንጠልጥሎ
ያሳድጋል አቀባብሎ
ቢንቀሳቀስ ቡድንን አዝሎ
እንዴት ይኖራል በአንድነት ተቻችሎ
በወግ በማዕረግ ይያዝ ነበር ተስተውሎ::

ግፈኛው አረመኔ ፈገግ ይላል
ሲበትነን ደስ ይለዋል
እርካታ ይሰማዋል
በርሱ ዘመን ማን ሊዛመድ

ሲገነዘብ የሰው ወኔ ተበርዞ
በእጅ አዙር አስጠምዝዞ
ሲረሽነን ጦሩን መዝዞ
እጅ ለእጅ ተያይዞ::

እናንት ትናንሽ አረመኔዎች
ዝዋይ የለ ብር ሸለቆ
እልፍ አዕላፍ ደሆችንም
አንጡራ ሃብቱን ሲሚጥጡት
ጥሪታችን ወደ ውጭ ባንክ
አንጀት አርስ መድኅኒቱን

ለቀቅ አርጉን እንቅፋት ሆናችኋል
ያጋዛችሁት ተመዝግቧል
በማታላል ዘርፋችኋል::
ሕዝቡ በቁጭት አንጀቱ አሯል
መሸሸቱን አገር አውቋል
ተመካክሮ አገር ቆርጧል::

ርዕዮትን አስደግፎ
በጋራ ተከባብሮ እንዳይወሰን
ርዕዮቱ ሳይሆን መጠይቁ
የትም ሃገር ሕዝቡ ነፃ ሊሆን

ፍላጎቱን አንፀባርቆ
ከልክሎና አጨናንቆ
ማን ይጠቀም ማን ተነጥቆ
ፍልሚያ ገጥሟል ተነቃንቆ::

ጊንጥ ሲነድፍ እስር አርገው
ሰይጣን ሲወር እንዲያጠምቁ
ጋኔሉ እንዲወገድ
እርቃኑን ሲዠልጡት

ይበጡታል መርዙ እንዲፈስ
ካኮርማጅ ጋር ያመጧል ቄስ
መለኮታዊ ኃይል ያሠርፃል ፈውስ
ይለቀዋል እርኩስ መንፈስ::

አትርሱ ሲናዘዝ መመዝገቡን
ባገር ክህደት ይከሰሳል
የብሌርን እፁብ-ድንቁን
በግልጽ ይውጣ በድህረ-ግፅ

ጭንቅ ወጥሮት ሲለፈልፍ
የቡሽ አጋር በሠራው ግፍ
ሁሉም ይወቅ ዘረኛውን
ዓለም ያንብ ጉዳቸውን::

በየት ዘመን በማን ሃገር
አማራጩን ላለማየት
ሰባአዊነት የሚዋረደው
መሠረታዊ ሃቅን መቀበል

እነማን አለፉ ዕምነት ሳይኖራቸው
ዝግት አርገው ስላልሆነ ፈቃዳቸው
ግፍና ዘረኝነት የሚነግሰው
ሲሳነን ነው ሚበላሸው::

እንቅልፍ የለኝ እንዳልተኛ
ፍቅረ-ወሰላም ሲወርድማ
በነፃነት ማሰብ ካልቻልኩ
ተንቀጥቅጦ ፈርቶ መኖር

ተከልክዬ ባረመኔ
ሕልም አያለሁ ለወገኔ
ሃገር አለኝ አልል እኔ
ትርጉም አይሰጥ ሕይወት ለእኔ::

አይቀርም ጊዜ ያነሳዋል
መሪ ሃሳብ ስለያዝነ
አንሰማም ግፈኞችን
የኛ ሃሳብ ቢጣል ዛሬ
ፍንክች አንል በርሱ ወሬ
ከዘረኞች የለም ፍሬ::

እንስሳት ሲባዙ ብቻ ሳይሆን
እንዲያድግ የሚደረግ
ካልተፋጨ ካልተጋጨ
አገር ይድናል ብዬ አልልም
ወዳጅን ማስተናገድ
የሃሳብም ፅንስ አለው
ተኮትኩቶ ባገሬ ሰው
ሕዝበ-ገዝነትን ላይጥስ ተማምሎ
ልኩን ሳያውቅ አሰላስሎ
መጀመሪያ ጠላት ጥሎ::

ሕዝብ ተርቦ ሕዝብ ታሞ
ከሃዲ ግፈኞች በሸወዳ
ሕዝብን በሕዝብ ያስነሳሉ
የአዳምን ፍጡር አሸበሩት
ሲቆራመድ እየተሳለቁ
ዲሞክራሲን እያሳበቁ
ያገርን ሃብት እንዲሰርቁ
ስልጣኒቱን እንዳይለቁ::

ግፍኛው ዘውዱን ጫነ
ሰላም የለም ልቡ ያውቃል
ጀግኖች ናቸው ሚፋለሙት
በቆራጥነት ሚዋደቁት
ተዋርዶ ከሚያዋርድ
ሕዝባችን ግን ተገፏል ነጻነቱ
ይቀጥላል በጥፋቱ::
ገና ከጥንት ከጠዋቱ
ምንም ቢበዛ እንቅፋቱ
ይሠውረነ ከመዓቱ::

የናታችን ማህፀኗ ነጥፎ አያውቅ
ብዙ ተባዙ የሚለውን
ቃሉ ስጋ ሆኖ እኛን ወልደሽ
ዘንቦ ተባርቆ ውቃቤ የራቀው
ባልሠራሺው ሃጥያት
ስምሺን ያስጠፋዋል
ለርሱ ምርቃኑ ይንቀልህ!
እያንዳንዱ የራሱን ፅዋ
ዝንተ-ዓለም ስትራቢ
መለኮታዊ ቃል ስታስቢ
በማሳደግ ስትመግቢ
ትወልጃለሽ ሳትይ እንቢ::
ከአብርክሺ ወጥቶ
ምግባሩ በጣም ከፍቶ::
ያጥፋህ! ነው የሚባለው በይፉ
ፍልቅ ፍስስ አርጎ እየደፉ::

ደጋግና ብልህ ልጆች
የናት ሆድ ዝንጉርጉር
እንተ ሆየ ያሁኑስ ፅንስ
እየጠበባት መቆም ሆነ
እርግጫውም ሆነ ጡጫው
አድጎ ገዝፏል
ጭንቅ አማላጅቱ
ነገር ግን በመውለጃሽ ዕለተ ቀን
እንደነበራት የሚረዱት
ይላሉ ያለፉና ያገደሙት::
ዕድገቱ ለየት ይላል አለች
መቀመጡን ስላልቻለች::
በርታ ብሏል የሆድሽ ፍሬ የሽሉ
አለዝያም መንትያዎች ይሆናሉ::
እግዝእትነ ማርያም ትከተልሽ እማማ
ያ ዓርዮስ እንዳይሰማ::

በልጆችዋ ባላሚወች
ኢትዮጵያ እንደገና
ይልቅስ ሰብሰብ በሉ
ለብትረ-ስልጣንና ለንዋይ በማይሳሱ
እንደምትወለድ አይቀሬ ነው እንዳትረሱ
ሙያተኛ አዋላጆች እዩት ገፍቷል ፅንሱ::

By: Cosmos-2000
Stockton, June, 2009